# ዜና አመዝኮ



የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን፣ ቅፅ 11 ቁጥር 2 መጋቢት/ሚያዚያ 1997

## በዚህ እትም ውስጥ

ባለፉት 4 ወራት ከ1.1 ሚሊዮን ኩንታል በላይ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ተከፋፍሏል
*ገጽ 2*

ኢ.ኤ.አ ለ2005 ዓ.ም ከቀረበው የዕርዳታ ጥያቄ ውስጥ 314 ሺህ 42 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ተገኝቷል
*ገጽ 3*

በደቡብ ክልል በሰዎች የኑሮ መሠረት ላይ በተካሄደው ጥናት ላይ ውይይት ተካሄደ
*ገጽ 3*

የአየር ሁኔታዎች መድህን ዋስትና በአደጋ ጊዜ ፈጣን ምላሽ ለማስገኘት የበለጠ ሊረዳ እንደሚችል ተገለፀ
*ገጽ 5*

በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሀዛዊ መረጃ ትንተና ላይ ያተኮረ ሥልጠና ተሰጠ
*ገጽ 6*

የተረጂ ሕዝብ ቁጥርና የሚያስፈልገው ዕርዳታ መጨመሩ ተመለከተ
*ገጽ 7*

# በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ዕርዳታ በመቅረብ ላይ ይገኛል::

በሱማሌ ክልል በጎዴ ፣ አፍዴር እና ቆራሔ ዞኖች በሚገኙ በተለያዩ ወረዳዎች የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ሙላት ባስከተለው የጎርፍ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ ወገኖች ልዩ ልዩ የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ዕርዳታዎች በመቅረብ ላይ ይገኛሉ::



በደጋው የሀገሪቱ አካባቢ በዘነበው ከፍተኛ ዝናብ ሳቢያ የሸበሌ ወንዝ ሞልቶ ከሚያዝያ 16 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ በሱማሌ ክልል በጎዴ ዞን ምሥራቅ ኢሚ ፣ ቀላፎ ፣ ሙስታሒል፣ ጎዴ እና ፌርፌር ወረዳዎች ፣ በአፍዴር ዞን ደግሞ በምዕራብ ኢሚ ወረዳ እንዲሁም በቆራሔ ዞን ቀብሪደሀር ወረዳዎች በሚገኙ 190 መንደሮች በደረሰው መጠነ ሰፊ የሆነ የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ ሳቢያ ከ80 በላይ ሰዎች መሞታቸው ፣ 4 ሺህ 778 ሰዎች መፈናቀላቸውን እንዲሁም 1 ሺህ 200 ቤቶች መውደማቸውን ፣ 6 ሺህ 500 በላይ የቤት እንስሳት ፣ ከ19 ሺህ በላይ ዶሮዎች ፣ ሦስት የመስኖ ጠምፖች በርካታ ንብረቶች በጎርፍ መወሰዳቸውን ወደ ሥፍራው ከተንቀሳቀሰው አጥኚ ቡድን ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል:: ከዚህ በተጨማሪ 264 ሄክታር መሬት ሰብል በጎርፉ ሳቢያ መውደሙን ፣ 1ሺህ 692 ኩንታል የበቆሎ ክምችትም ከጥቅም ውጪ መሆኑም ታውቋል::

የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን አደጋው ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በተለይ ችግሩ በከፋባቸው የምስራቅና ምዕራብ ኢሚ ወረዳዎች ላይ ከመከላከያ ሚ/ር በተገኙ ሁለት ሔሊኮፕተሮች አማካይነት ለተጎጂዎቹ አስፈላጊውን ዕርዳታ አቅርቧል:: ከዚሁ በተጨማሪ ከኮሚሽኑ፣ ከክልሉ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ቢሮ ፣ ከዞኑ አመዝ ቢሮና ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ መ/ቤቶች የተውጣጡ ሙያተኞች ከኢትዮጵያ አየር ኃይል ጋር በመቀናጀት የአደጋውን ሁኔታ በቅርብ በመከታተልና የዕርዳታ አቅርቦቱን በማስተባበር ረገድ በታየው እንቅስቃሴም ችግሩን በሚገባ ለመቋቋም አስችሏል:: በዚሁ መሠረት ኮሚሽኑ እስከ ሚያዝያ 24 ቀን 1997 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ችግሩ ለደረሰባቸው አካባቢዎች 200 ኩንታል የምግብ እህል፣ 275 ኩንታል ብስኩት ፣ 65 ኩንታል አልሚ ምግብ እንዲሁም 7 ሺህ 16 ብርድልብስ ፣ 6 ሺህ 500 ኘላስቲክ ሳህኖች፣ 5 ሺህ 500 ኘላስቲክ ኩባያ ፣ መጠናቸው 4 ሜትር በ 50 ሜትር የሆኑ 204 ጥቅል የመጠለያ ኘላስቲክ ሽቶች ፣ 3 ሺህ 500 ኘላስቲክ ጆጎችን ከድሬደዋ ጎዴ ድረስ ከሀገር መከላከያ በተገኘ አውሮኘላን ጉዳቱ ወደደረሰባቸው አካባቢዎች በሁለት ሔሊኮኘተሮች አማካይነት ለተጎጂዎች በማድረስ

ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዋችንና ሌሎች ተገዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣www.dppc.gov.et

እንዲከፋፈል ተደርጓል።

ይኸው የዕርዳታ አቅርቦት በጎርፉ ተጎጂ የሆኑትን የቀላፎ ፣ ሙስታሒል ፣ ፌርፌር እና ቀብሪበያህ ወረዳዎችንም የሚያጠቃልል መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።



ከአጥኚው ቡድን የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው በአሁኑ ወቅት በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የጎርፉ መጠን በመቀነሱ ከሙስታሂል ከተማና ከጎርፉ በውኃ ከተከበቡ ቦታዎች በስተቀር በተሽከርካሪና በጋማ ከብቶች ለተጎጂዎቹ ድጋፍ ለማቅረብ ይቻላል።

ሆኖም ከጤናና ከአካባቢ ንፅህና ጋር የተያያዙ እንደወባ ፣ ተቅማጥና /ሌሎችም ውኃ ወለድ በሽታዎች/ ከመተንፈሻ አካላት ጋር የተያያዙ በሽታዎች የመከሰት ሥጋት መኖሩ ተመልክቷል።

ይህንን ችግር ለመቋቋም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 19 የአስቸኳይ ጊዜ የህክምና መረጃ ቁሳቁሶችንና መድሃኒቶችን መላኩንና በቀጣይም ሁኔታውን በቅርብ የሚከታተሉ የጤና ባለሙያዎች ቡድን ችግሩ ወደተከሰተባቸው አካባቢዎች ለማንቀሳቀስ በዝግጅት ላይ እንደሆነም ታውቋል።

## ባለፉት 4 ወራት ከ1.1 ሚሊዮን ኩንታል በላይ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ተከፋፍሏል



ከጥር ወር እስከ ሚያዝያ 1997 ዓ.ም ባሉት አራት ወራት ውስጥ 1 ሚሊዮን 112 ሺህ 212 ኩንታል ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 1 ሚሊዮን 94 ሺህ 302 ኩንታል በኮሚሽኑ ቀሪው 17 ሺህ 910 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ቀረበ ።

በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ፈላጊ ወገኖች ከጥር ወር እስከ ሚያዝያ 1997 ዓ.ም ባሉት አራት ወራት ውስጥ በጠቅላላው 1.1 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ተመድቦ መከፋፈሉ እና በመከፋፈል ላይ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።

በእነዚሁ ወራት በየክልሎች ለሚገኙ ተረጂ ወገኖች ከተሰራጨው 1 ሚሊዮን 112 ሺህ 212 ኩንታል ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 1 ሚሊዮን 94 ሺህ 302 ኩንታል በኮሚሽኑ ቀሪው 17 ሺህ 910 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት የቀረበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

ለየክልሎቹ የሚመደበው የምግብ ዕርዳታ መጠን በየክልሎቹ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት የሚለያይ ሲሆን በዚህ መሠረት ከጥር እስከ ሚያዝያ ባሉት ወራት በድምሩ ከተመደበው 1 ሚሊዮን 112 ሺህ 212 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለሱማሌ 194 ሺህ 239 ኩንታል፣ ለአፋር 349 ሺህ 496 ኩንታል ፣ ለትግራይ 208 ሺህ 894 ኩንታል ፣ ለኦሮሚያ 227 ሺህ 648 ኩንታል እና ለጋምቤላ 16 ሺህ 872 ኩንታል ፣ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች 92 ሺህ 360 ኩንታል እና ለድሬደዋ መስተዳድር 6 ሺህ 530 ኩንታል ተመድቦ ለተረጂ ወገኖች ተከፋፍሏል።

ለሚያዝያ ወር ከተመደበው 346 ሺህ 370 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለአፋር 95 ሺህ 720 ኩንታል ፣ ለኦሮሚያ 96 ሺህ 720 ኩንታል ፣ ለትግራይ 72 ሺህ 130

ኩንታል ፣ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች 67 ሺህ 170 ኩንታል ፣ ለድ ደዋ 8 ሺህ 420 ኩንታል ፣ እና ለሱማሌ 6 ሺህ 210 ኩንታል መሆኑም ታውቋል:: ለሚያዝያ ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 337 ሺህ 430 ኩንታል በኮሚሽኑ ቀሪው 8 ሺህ 950 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት የተመደበ ነው::

## እ.ኤ.አ ለ2005 ዓ.ም ከቀረበው የዕርዳታ ጥያቄ ውስጥ 314 ሺህ 42 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ተገኝቷል



እ.ኤ.አ በ2005 ዓ.ም በታህሳስ መጨረሻ ከተጠየቀው 396 ሺህ 782 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በጠቅላላው 314 ሺህ 42 ሜ/ቶን የተገኘና ቃል የተገባ መሆኑ ታውቋል::

እ.ኤ.አ በ2005 ዓ.ም አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች እ.ኤ.አ በታህሳስ መጨረሻ ከተጠየቀው 396 ሺህ 782 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በጠቅላላው 314 ሺህ 42 ሜ/ቶን የተገኘና ቃል የተገባ መሆኑ ታውቋል::

ከዚሁ በለጋሽ ሀገራትና ድርጅቶች ከተገኘውና ቃል ከተገባው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 34 ሺህ 24 ሜ/ቶን በ2004 ዓ.ም ከነበረው የዕለት ዕርዳታ ክምችት የተላለፈ፣ 71 ሺህ 815 ሜ/ቶን በ2004 ቃል ተገብቶ ወደ 2005 የተላለፈ ሲሆን ቀሪው 208 ሺህ 203 ሜ/ቶን በ2005 ዓ.ም ውስጥ አዲስ ቃል የተገባ መሆኑ ታውቋል::

እ.ኤ.አ. በ2005 ዓ.ም አዲስ ቃል ከተገባው 208 ሺህ 204 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ የአሜሪካን መንግሥት በዓለም ምግብ ኘሮግራም ፣ በመያዶች እና በመንግሥት በኩል በድምሩ 113 ሺህ 645 ፣ የአውሮጠ ሕብረት በአመዝኮ በኩል 45 ሺህ ሜትሪክ ቶን ፣ በዓለም ምግብ ኘሮግራም በኩል 28 ሺህ 721 ሜ/ቶን ፣ የኢጣሊያ መንግሥት በለገሠው 2 ሚሊዮን ዩሮ የሚገዛ ግምቱ 9 ሺህ ሜ/ቶን የምግብ እህል ፣ የጃጠን መንግሥት በለገሠው 2 መቶ ሚሊዮን የን የሚገዛ ግምቱ 6 ሺህ ሜ/ቶን የምግብ እህል፣ ሰዎች ለሰዎች የተባለው ግብረ ሰናይ ድርጅት 4 ሺህ 928 ሜ/ቶን የእስፔይን መንግሥት በዓለም ምግብ ኘሮግራም ና በአመዝኮ በኩል 845 ሜ/ቶን እና የግብፅ መንግሥት በአመዝኮ በኩል 64 ሜ/ቶን የምግብ እህልና አልሚ ምግብ ለግሰዋል:: እ.ኤ.አ ከ2004 ዓ.ም ከነበረው ክምችትና ቃል ተገብቶ ከተሸጋገረው እንዲሁም እ.ኤ.አ በ2005 ቃል ከተገባው 314 ሺህ 42 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 245 ሺህ 791 ሜ/ቶን የምግብ እህል ፣ 33 ሺህ 582 ሜ/ቶን አልሚ ምግብ ፣ 12 ሺህ 968 ሜ/ቶን ዘይት ፣ ቀሪው 21 ሺህ 701 ደግሞ ጥራጥሬ መሆኑ ታውቋል::

## በደቡብ ክልል በሰዎች የኑሮ መሠረት ላይ በተካሄደው ጥናት ላይ ውይይት ተካሄደ

አደጋ በሚከሰትበት ወቅት የሰዎች የኑሮ መሠረት ሳይናጋ ተገቢውን ወቅታዊ ድጋፍና ምላሽ ለመስጠት በሚያስችሉ ስልቶች ላይ በማተኮር በደቡብ ብሔር ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የተለያዩ አግሮ ኢኮሎጂ ባላቸው 22 ወረዳዎች በተካሄደው የመጀመሪያ ዙር ቅኝት ጥናት ግኝት ላይ የተወያየ ስብሰባ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሚያዝያ 12 ቀን 1997 ዓ.ም ተካሄደ::

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ፣ በደቡብ ብሔር ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና

ቢሮዎች ባለሙያዎች አማካኝነትና በፊውስ ኔት ዩ ኤስ ኤይድ የቴክኒክ ድጋፍ በመካሄድ ላይ የሚገኘው ጥናት ዓላማ ሊተነበዩ ለሚችሉና ለማይችሉ አደጋዎች መንስዔዎች ፣ የተሻሻሉ የአደጋ ጥናት ስልቶችን በመጠቀም አፋጣኝ ውጤታማ ምላሽ ለመስጠት የሚቻልበትን ዘዴ መቀየስ መሆኑ በስብሰባው ላይ ተገልጧል።

ክፍሎች ለሚካሄድ ጥናቶች የሚሰጠው ጠቀሜታ የጎላ እንደሆነም ተብራርቷል።

በስብሰባው ወቅት በተሰጡት አስተያየቶች እንደተጠቆመው ጥናቱ በዓይነቱ አዲስ ከመሆኑ ባሻገር ከተለመደው የምግብ አቅርቦትና ምርት ላይ ካተኮረ አጠናን ወጣ ብሎ የሰዎችን የኑሮ መሠረት መነሻ



*የጥናቱ ዓላማ ሊተነበዩ ለሚችሉና ለማይችሉ አደጋዎች መንስዔዎች ፣ የተሻሻሉ የአደጋ ጥናት ስልቶችን በመጠቀም አፋጣኝ ውጤታማ ምላሽ ለመስጠት የሚቻልበትን ዘዴ መቀየስ መሆኑ በስብሰባው ላይ ተገልጧል።*

የጥናቱ ውጤት በየወረዳዎቹ ያለውን የእርሻና የእንስሳት ሁኔታ ፣ የምግብ አቅርቦትና ልውውጥ ፣ በማመላከት የምግብ ኢኮኖሚ ትንተና ለማካሄድ ፣ ከነዋሪዎቹ የኢኮኖሚ አቅም በመነሳት የነዋሪዎቹን ገቢና ወጪ ይዞታ በመተንተን ከተለያዩ ለአደጋ ከሚያጋልጡ መንስኤዎች ጋር አጣምሮ በማጥናት የተጠናቀረው መሠረታዊ መረጃ የሰዎችን የኑሮ መሠረት ለመቀየርና ለማሻሻል ብሎም አደጋ በሚከሰትበት ወቅት የኑሮ መሠረታቸው ሳይናጋ ተገቢውን ወቅታዊ ድጋፍ በማድረግ ረገድ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ጥናቱ የየወረዳዎቹን መልክዓ ምድራዊ የምርት ይዞታና ኢክኖሚ በማካተት በናሙናነት በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ያለውን የአኗኗር ሁኔታ ዝርዝር ትንተና በመያዙ ለክልሉ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት መጠናከርና ለሌሎች የልማት ሥራ ጥረቶች ግብአት ሊሆን እንደሚችል ታውቋል። በተጓዳኝም የጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ግቃት በተመሳሳይ በክልሉ ላሉት ወረዳዎች ፣ በሂደትም በሌሎች የሀገሪቱ

በማድረግ ነዋሪዎች በራሳቸው አደጋን ለመቋቋም ባህልን በማጎልበት ከሚሰጧቸው ድጋፎች ጋር አጣምሮ ለመተግበር የሚያስችል መሠረታዊ መረጃዎችን ማጠናቀሩ በቀጣይ ለሚወሰዱ ሁለገብ እርምጃዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። በአስተያየቶቹ ጥናቱ ይበልጥ ሊጎለብት የሚችልበትን ገንቢ ሃሳቦችንም አቅርበዋል።

ይህ በዓይነቱ አዲስ የሆነውና የሰዎችን የኑሮ መሠረት በቤተሰብ ደረጃ በመተንተን ላይ ያተኮረው ጥናት ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ለምግብ ዋስትና ቢሮ ስትራቴጂካዊ ግቦች ስኬትም ሁነኛ ድርሻ እንደሚያበረክትም ተመልክቷል።

በስብሰባው ላይ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሲሞን መቻለን ጨምሮ ከአመዝኮ ፣ ከተመድ ፣ ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶችና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

# የአየር ሁኔታዎች መድህን ዋስትና በአደጋ ጊዜ ፈጣን ምላሽ ለማስገኘት የበለጠ ሊረዳ እንደሚችል ተገለፀ

በአየር ሁኔታዎች መዛባት ምክንያት የድርቅ አደጋ በተደጋጋሚ በሚከሰትባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች ለችግሩ ተጋላጭ ለሆኑ ወገኖች ፈጣን የአደጋ ጊዜ ምላሽ በማስገኘት ረገድ የአየር ሁኔታ መድህን ዋስትና (Weather Insurance) የበለጠ ሊረዳ እንደሚችል ተመለከተ::

በሀገራችን ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የምግብ ዋስትና ኘሮግራም የአየር ሁኔታ መድህን ዋስትና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነ የጠቆሙት ኮሚሽነር ሲሞን ይኸን አዲስ ሀሳብ ቀስ በቀስ እንዲታወቅና በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሀሳቡ አመንጪ ባለቤቶች ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው



አሳስበዋል:: ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሀገራችን ባለሙያዎችም ለዚሁ እውንነት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባቸዋል ብለዋል:: አያይዘውም ሀሳቡን ለማስተዋወቅ ጥረት ያደረጉትንና ዐውደ ጥናቱን ያዘጋጁትን የዓለም ምግብ ኘሮግራም እና የዓለም ባንክን አመስግነዋል::

ይኸ የተመለከተው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ፣ የዓለም ምግብ ኘሮግራም እና የዓለም ባንክ በጋራ ባዘጋጁትና መጋቢት 5 እና 6 ቀን 1997 ዓ.ም በኮሚሽኑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተካሔደው የአየር ሁኔታ ኢንሹራንስ ዐውደ ጥናት ላይ ነበር::

በዚሁ ዐውደ ጥናት መክፈቻ ላይ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ እንደተናገሩት የአየር ሁኔታ መድህን ዋስትና ፅንሰ ሀሳብ በአንዳንድ ሀገሮች እየተሠራበት ያለ ሊሆን ቢችልም በሀገራችን አዲስ ሀሳብ እንደመሆኑ ተግባራዊ ለማድረግ ጊዜ ሊወስድ ይችላል:: ይሁን እንጂ ተግባራዊ ቢደረግ በተለይ በድርቅ አደጋ በተደጋጋሚ ለሚጠቃው የሀገራችን አርሶ አደር የፈጣን የአደጋ ጊዜ ምላሽ ለማስገኘት የሚያስችል ጠቃሚ ሃሳቦችን አካቷል ብለዋል::

በዐውደ ጥናቱ ላይ እንደተገለጸው የአየር ሁኔታ መድህን ዋስትና ዓላማዎች ወቅታዊ የአደጋ ጊዜ ምላሽ መስጠት ማስቻል ፣ የአደጋ ጊዜ ምላሽ በልግስና መልክ ከሚደረግ ይልቅ ህጋዊ አሠራርን የተከተለ መብት እንዲሆን ማድረግ እና የአደጋ ጊዜ ምላሽን ለማሻሻል የሚያስችሉ መሠረቶችን ማስፋት የሚሉት ናቸው::

በዐውደ ጥናቱ አቅራቢዎች እንደተመለከተው የአየር ሁኔታ መድህን ዋስትና ተጠቃሚ የሚሆኑት በተለያዩ መጥፎ የአየር ሁኔታዎች በምርት መቀነስና መጥፋት ሳቢያ ለአደጋ

የሚጋለጡ አርሶ አደሮች ናቸው:: አርሶ አደሮችን ለአደጋ የሚያጋልጡ መጥፎ የአየር ሁኔታዎች ብዙ ዓይነት ቢሆኑም በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ አርሶ አደሩን ለምግብ እጥረት አደጋ የሚያጋልጠው መጥፎ የአየር ሁኔታ ድርቅ ሲሆን፣ በድርቅ ሳቢያ የሚከሰተውን የምግብ እጥረት ለመቋቋም ኢትዮጵያ የምግብ ዕርዳታ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ስታገኝ ዓመታት ተቆጥረዋል:: በዚህ ዓይነት በአደጋው ተጠቂ ለሆኑት ወገኖች የሚደርሰው የምግብ ዕርዳታ የተጠቂዎቹን ሕይወት ከማትረፍ ባሻገር በዘላቂነት ከችግሩ ሙሉ በሙሉ ለመውጣት አያስችላቸውም:: በመሆኑም በድርቅ አደጋ ለሚጠቁ አርሶአደሮች የአየር ሁኔታ መድህን ዋስትና በመግባት አስተማማኝ ወቅታዊ የአደጋ ጊዜ ምላሽ በማስገኘት ብሎም አርሶአደሩ ጥሪቱን ይዞ በመቆየት በቀጣዩ የምርት ወቅት ሙሉ ሀይሉንና ሀሳቡን በግብርና ሥራው ላይ በማዋል በራሱ እንዲቆም ያስችለዋል ተብሎ እንደሚታመን ተብራርቷል::

የአየር ሁኔታ መድህን ዋስትና እንደሌሎች የመድህን ዋስትናዎች ሁሉ በራሱ ሕግና አሠራር መሠረት ተግባራዊ የሚደረግ ስለመሆኑም እንደአብነት በህንድና በቦትስዋና የተገኘን ልምድ በማጣቀስ ከአቅራቢዎች ሠፊ ማብራሪያ ተሰጥቷል::

ከአመዝኮና ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፣ ከረድኤትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ ከ40 በላይ የሚሆኑ ባለሙያዎች ተሳታፊ በሆኑበት በዚህ ዐውደ ጥናት የአየር ሁኔታ መድህን ዋስትና ጽንሰ ሀሳብን በኢትዮጵያ ተግባራዊ ማድረግ በሚቻልባቸው ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ሠፊ ውይይት ተካሂዷል::

## በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሀዛዊ መረጃ ትንተና ላይ ያተኮረ ሥልጠና ተሰጠ

ከሁሉም ክልሎች ለተውጣጡ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ባለሙያዎች በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አኃዛዊ /ዳታ/ ትንተና ላይ ያተኮረ ሥልጠና ከመጋቢት 12 እስከ መጋቢት 22 በናዝሬት አዳማ ራስ ሆቴል ተሰጠ::

በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መምሪያ የሰብል ጥናት ቡድን እንደተገለጸው ሥልጠናው በየጊዜው የሚሰበሰቡ የቅድሚያ ማስጠ ንቀቂያ መረጃዎችን ብዛትና ጥራት በማሻሻል በሪፖርት አቀራረብ ፣ በመረጃ አሰባሰብና ትንተና ላይ ባለሙያዎችን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታስቦ የተዘጋጀ ነው::

በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መምሪያ የሰብል ጥናት ቡድን እንደተገለጸው ሥልጠናው በየጊዜው የሚሰበሰቡ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን ብዛትና ጥራት በማሻሻል በሪፖርት አቀራረብ ፣ በመረጃ አሰባሰብና ትንተና ላይ ባለሙያዎችን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታስቦ የተዘጋጀ ነው::

ሠልጣኞች መምሪያው በሚጠቀምባቸው ፣ በሰብልና በእንስሳት ሁኔታ ጥናት ፣ በገበያ ክትትልና ግምገማ ፣ በአካባቢ የምግብ ዋስትና ማንዋሎች ላይ በቂ ግንዛቤ አግኝተው ወደ የክልላቸው በሚሄዱበት ጊዜ እነዚህኑ ማኑዋሎች በመጠቀም ጥራትና ብቃት ያለው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ረገድ ያለውን ችግር ያቃልላሉ ተብሎ ይጠበቃል::

ይኸው 25 የሚሆኑ ሰልጣኞች የተሳተፉበት ሥልጠና የተዘጋጀው ከተመድ ህፃናት መርጃ ድርጅት /ዩኒሴፍ/ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ መሆኑ ታውቋል::

በሌላም በኩል ከመጋቢት 20 እስከ 22 ቀን 1997 ዓ.ም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ዓመታዊ ምክክር መድረክ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የህፃናት መርጃ ድርጅት ጋር በመተባበር መዘጋጀቱን የቅድሚያ ማስጠ

ንቀቂያ መምሪያ አስታውቋል።

መምሪያው እንዳስታወቀው መድረኩ በዩኒሴፍ ድጋፍ በፌዴራልና በክልሎች በጋራ በሚካሄዱ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ተዛማጅ ሥራዎችን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በገመገመው ዓመታዊ የምክክር መድረክ ላይ ፣ የየክልሎቹ የፋይናንስ ሃላፊዎች ፣ ዩኒሴፍ ፣ በእንግሊዝ ሕፃናት አድን ድርጅት የአቅም ግንባታ ኘሮጀክትና የዩናይትድ ስቴትስ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት /ዩ.ኤስ.አይ.ዲ/ ተሳታፊ ሁነዋል።

## የተረጂ ሕዝብ ቁጥርና የሚያስፈልገው ዕርዳታ መጨመሩ ተመለከተ

እ.ኤ.አ በ2005 ቀደም ብሎ ተይዞ ከነበረው የተረጂ ሕዝብ ቁጥርና የሚያስፈልገው ዕርዳታ መጨመሩ ተመለከተ።

ይህ የተመለከተው ሚያዝያ 27 ቀን 1997 ዓ.ም በአመዝኮ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የፌዴራል አመዝኮና የሰብዓዊ ዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በጋራ ባቀረቡት የዕርዳታ ጥያቄ ሰነድ ላይ ነው። በሰነዱ ላይ እንደተገለጸው የተረጂው ቁጥር በ687 ሺህ 470 ጨምሮ ከ3.1 ሚሊዮን ወደ 3.8 ሚሊዮን ከፍ ያለ ሲሆን የሚያስፈልገው ዕርዳታ ደግሞ በ66 ሺህ 198 ሚሊዮን ጨምሮ በጠቅላላ የሚያስፈልገው ዕርዳታ ወደ 464 ሺህ 385 ሜ/ቶን መድረሱ ተመልክቷል።

የተረጂው ቁጥር በ687 ሺህ 470 ጨምሮ ከ3.1 ሚሊዮን ወደ 3.8 ሚሊዮን ከፍ ያለ ሲሆን የሚያስፈልገው ዕርዳታ ደግሞ በ66 ሺህ 198 ሜትሪክ ቶን ጨምሮ በጠቅላላ የሚያስፈልገው ዕርዳታ ወደ 464 ሺህ 385 ሜ/ቶን መድረሱ ተመልክቷል።

ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ፍላጎቶችን በተመለከተም በግብርና ፣ የአደጋ ምላሽ አቅም ግንባታንና የማስተባበር አቅምን ለማጎልበት የሚያስፈልገው የዕርዳታ ፍላጎት ጭማሪ ያላሳየ ቢሆንም ፣ ለጤናና ሥነምግብ ፣ ለውሃና ለአካባቢ ንፅሕና ጥበቃ አገልግሎት በድምሩ 24 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የዕርዳታ ፍላጎት ጭማሪ ማሳየቱ ተገልጿል። የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ጥያቄም ሆነ የሴፍቲኔት ኘሮግራም ማስፈጸሚያ ፈንድ በመጀመሪያዎቹ 3 ወራት ውስጥ በወቅቱ ምላሽ ባለመገኘቱ ሳቢያ እና የምግብ እጥረት በተጋለጡ አንዳንድ አካባቢዎች የተረጂው ቁጥር በመጨመሩ ለዕርዳታ ፍላጎቱ መጨመር ዋንኛ ምክንያት እንደሆነም ተመልክቷል።

በሰነዱ እንደተመለከተው እስካሁን ድረስ ቃል የተገባውንና የደረሰውን ዕርዳታ ግምት ውስጥ በማስገባት ግምቱ 66 ነጥብ 2 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሆነ ወደ 165 ሺህ 510 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ለቀሪዎቹ ወራት የሚያስፈልግ ሲሆን ፣ ምግብ ነክ ባልሆኑ ዕርዳታዎች በኩልም በጠቅላላ ከሚያስፈልገው 135 ነጥብ 6 ሚሊዮን ውስጥ 30 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብቻ የተገኘ በመሆኑ ቀሪውን 135 ነጥብ 5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሟላት ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ተገልጿል።

የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር የተከሰተውን የምግብ እጥረት ለመቋቋም መንግሥት በመውሰድ ላይ ያለውን እርምጃና የተረጂው ሕዝብና የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የዕርዳታ ፍላጎት የሚያጠኑ የተለያዩ አካላት ያሉባቸው የጥናት ቡድኖች ወደ ክልሎች መሰማራታቸውንና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እና ለዓለም ህብረተሰብ እንዲያውቀው እንደሚደረግ ሚያዝያ 12 ቀን 1997 ዓ.ም ለሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ማሳወቃቸው ይታወሳል።